# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

***መጋቢት 1 ቀን 2005 ዓ.ም.***

**በወያኔ ውስጠ የእርሰ በርሰ ክፍፍሉ ተፋፍሟል ይባላል**

**የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቲ አባሎች እና ከፍተኛ ባለስልጣናት የድርጅቱን ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳን በጥያቄ አፋጠጡት፤**

**በባህር ዳር ከተማ ለሚደረገው ጉባኤ በከተማዋ ያሉ መለስተኛም ሆነ ትላልቅ ሆቲሎች ሌሎች እንግዶችን እንዳያስተናግዱ ተከለከሉ፤**

**ወያኔ በቦንድ ስም ከግል ባንኮች 15 ቢሊዮን ብር ወሰደ አሁንም ጨምሩ አለ፤**

**ንግድ ባንክ፤ ልማት ባንክ፤ ወጋገንና አንበሳ ባንኮች መዋጮው አይመለከታቸውም ተብሎ ሳያዋጡ ቀረ፤**

የሀገሪቱን ስልጣን ጠቅልሎ በያዘው በወያኔ ቡድን ውስጥ መለስ ዜናዊ ከሞተ በሁዋላ የእርስ በርስ ክፍፍሉ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱንና በሁለት ምድብ መሰንጠቁን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋለጠ፡፡

ወያኔ በ1993 ዓ.ም ባጋጠመው መሰንጠቅ ከፍተኛ ሽኩቻ ተፈጥሮ በሁለት ቡድን ተከፍሎ ሲፋለም እንደነበረው ግዜ ሁሉ አሁንም በድጋሚ ክፍፍል ተፈጥሮ አደጋ ውስጥ መውደቁን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማው ገልጾዋል፡፡

ወያኔ በሁለት ቡድን የተከፈለበት ዋነኛ ምክንያት ቀድሞ አፈንጋጭ የተባለው ቡድን እና የተባረረው የእነ ስዬ አብርሀ ወገን ይቅርታ ተጠይቆ ወደ ድርጅቱ ይመለስ የሚለው አንደኛ ውና ዋነኛው ሲሆን ሌላው ደግሞ መለስ ሕወሀትን ቀብሮት ነው የሞተው በሚለው ዙሪያ መግባባት በመጥፋቱ የተነሳ በሁለት ቡድን ተከፍለው እየተፋለሙ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በዚህም የተነሳ መለስ ድርጅቱን ጠብቆና ታድጎት የነበረ በመሆኑ ስሙ በክፉ ሊነሳ አይገባም ......እንዲሁም በህወሀት ክፍፍል ግዜ ከድርጅቱ የተባረሩት በአሁኑ ሰዓት ወደ ፓርቲው መመለሳቸው የመለስን አቋዋም መሻር በመሆኑና  ትልቅ አደጋ ሊያስከትል ስለሚችል አንቀበልም በማለት አቋዋም የያዙት በትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት እና በህወሀት ሊቀመንበር አባይ ወልዱ የሚመራ ቡድን  ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ መለስ ሕወሀትን ከመቼውም ግዜ በላይ ቀልዶበት ነበር.....የአንድ ሰው የበላይነትን ብቻ ያረጋገጠ አካሄድ ሲያራምድ የነበረ በመሆኑ ብዙ ጥፋቶችን አጥፍቶ ነው የሞተው....... በህወሀት ክፍፍል ወቅትም የተፈጠረው የስልጣን ጥያቄ እንጂ የድርጅታዊ ጉዳይ ባለመሆኑ በዛን ግዜ የተባረሩት አመራሮች ይቅርታ ተጠይቀው ሊመለሱና ህወሀትን ሊታደጉት ይገባል በሚል አቋዋም በመያዝ በሌላ ወገን የቆሙት በስብሀት ነጋና በሕወሀት ምክትል ሊቀመንበር ደብረጽን የሚመራው ቡድን እንደሆነ ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል።

በአሁኑ ሰዓት ሕወሀት እጅግ የተዳከመበት ሰዓት በመሆኑ በ1993 ዓ.ም በሕወሀት ክፍፍል ወቅት የተባረሩት ከፍተኛ አመራሮች ወደ ድርጅታቸው ይመለሱ የሚለው ጥያቄ ዋነኛ እንደሆነና ይሄንኑ ውሳኔ ለማግኘት ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ በመቀሌ ይጠራና እንነጋገርበት በማለት በስብሀት ነጋ የሚመራው ቡድን ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርብም በህወሀት ሊቀመንበር በአባይ ወልዱ የሚመራው ቡድን ግን አይሞከርም በማለት አቋዋም በመያዙ ልዩነታቸው ተካርሮ እንደሚገኝ የምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል።

በአባይ ወልዱ .....አዜብ መስፍን .....ሳሞራ የኑስ እና በሌሎችም የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት የሚመራው ቡድን መለስን ከመላዕክት በላይ አድርጎ እየሳለ በማስቀመጡ የተበሳጩት የእነ ስብሀት ነጋ ቡድን መለስ ሕወሀትንም..... ኢህአዴግንም... ሀገሪቱንም ቁልቁል ቀብሮ የራሱን ዝና እና ክብር ብቻ ሲገነባ የነበረ ግለኛ ነው በማለት መከራከሪያ የሚያቀርቡ ሲሆን በ1993 ዓ.ም በነበረው የህወሀት ክፍፍል ወቅት የጀርባ አጥንት ሆኖ መለስን ከውድቀት ያተረፈው የብአዴኑ አዲሱ ለገሰ በተመሳሳይ አሁንም የእነ አዜብ መስፍንን ቡድን እንዲታደግላቸው እየለመኑት መሆኑን ከደረሰን የምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል።

በአባይ ወልዱ የሚመራው ቡድን አዜብ መስፍን... ሳሞራ የኑስ....ትርፉ ኪዳነ ማርያም...ሀድሽ ዘነበ....አለም ገ/ዋህድ...በየነ ምክሩ...ተክለወይኒ አሰፋ..... የተባሉትን የህወሀት ባለስልጣናትን ያቀፈ እና ከጀርባቸው የኤርትራው ተወላጅ በረከት ስምኦን ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገላቸው የሚገኝ ሲሆን በሌላኛው ቡድን ውስጥ የታቀፉት ደግሞ ከፍተኛ የሀገሪቱ ቁንጮ ባለስልጣናት ያሉበት ስብሀት ነጋ...ዶ/ር ደብረጽን....አርከበ እቁባይ...አዲስ ዓለም ባሌማ....ቅዱሳን ነጋ(የስብሀት እህት).....ጸጋዬ በርሄ...አባዲ ዘሙ....ኃይለ ኪሮስ ገሰሰ.....ተክለብርሀን የተባሉት እንደሚገኙበት ምንጮቹ አብራርተዋል።

ከሁለቱ ቡድን እራሳቸውን ያገለሉትና መሐል ሰፋሪ የሆኑት የህወሀት ሰዎች እራሳቸውን ሽማግሌ አድርገው በማቅረብ ለማወያየት እና ችግሩን ለመቅረፍ እየሞከርን ነው በማለት እየዳከሩ ቢሆንም በሁለቱም ወገን ተቀባይነት ባለማግኘታቸው እስከ አሁን አንዳችም የረባ እንቅስቃሴ ሲያደርግ እንዳልታየ ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል።

እራሱን የሽማግሌ ቡድን ብሎ ሰይሞ የሚንቀሳቀሰውን አካል የሚመሩት ደግሞ ዶ/ር ቲዎ-ድሮስ አድሀኖም እና አምባሳደር ብርሀነ ገ/ክርስቶስ ሲሆኑ ሁለቱን ቡድኖች ለመሸምገል ከፍተኛ ዘመቻ መጀመራቸው ቢነገርም እስከ አሁን ድረስ አንዳችም ውጤት እንዳላገኙም ታውቆዋል።

ሽምግልና ስራ መስራት የምትችሉት ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ ስታደርጉ ብቻ ነው በማለት የእነ ስብሀት ነጋ ቡድን ጠንከር ያለ አቋዋም በመያዙ ሽማግሌዎቹ በመደናገጣቸው እራሳቸውን ከሁለቱም ቡድን አግልለው የዳር ተመልካች ለመሆን እንደተገደዱና በአሁኑ ሰዓትም አንዳችም እንቅስቃሴ ከማድረግ እንደተቆጠቡ ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል።

በ1993 ዓ.ም በተፈጠረው የህወሀት ክፍፍል ወቅት አፈንጋጭ በተባለው ቡድን ውስጥ ሲሳተፉ የነበሩና በሁዋላም መልሰው ቡድኑን ተገንጥለው ለመለስ ያደሩት አባይ ጸሐዬ እና ሀሰን ሺፋ በአሁኑ እንቅስቃሴ ወደ የትኛው ቡድን እንደወገኑ አለመታወቁንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

ነባር የህወሀት ባለስልጣናት ለሁለት ተከፍለው እየተፋለሙ ባለበት በዚህ ግዜ የህወሀት ወጣት ካድሬዎች ደግሞ ድርጅቱን ለመታደግ እድሜ ጠገብ ባለስልጣናት በጡረታ ሊሰናበቱ እና እንደ አዲስም ሊዋቀር ይገባል ይህ ካልሆነ ግን ድርጅቱ የከፋ አደጋ ያጋጥመዋል በማለት እየስጠነቀቁና እያስፈራሩ መሆናቸው ሌላ የህወሀት አደጋ መፈጠሩን የሚያመላክት ነው ተብሎዋል።

ወጣቱ የህወሀት ክፍል ከሁለቱም ወገን ሳይቀላቀል እራሱን ገንጥሎ ገለልተኛ በሆነ መልኩ እየተከታተለ የሚገኝ ቢሆንም ሕወሀትን ዘመናዊነት አላብሰን ለማስቀጠል ከተፈለገ ነባር እና አዛውንት ፖለቲከኞች በጡረታ ተሰናብተው በአማካሪነት ብቻ እንዲያገለግሉ ካልተደረገ የሚፈጠረው አደጋ ከባድ ሊሆን ይችላል በማለት እያስጠነቀቁ መሆናቸው እየተነገረ ይገኛል።

መጋቢት 14 ቀን 2005 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ በሚደረገው 9ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ህወሀትን ወክለው የሚሳተፉ ከፍተኛ አመራሮችን ለመምረጥ በሚደረገው ስብሰባ ላይም የእርስ በርስ ሽኩቻው አይሎ እንደሚወጣ ከወዲሁ ስጋት ያሳደረ ሲሆን በአባይ ወልዱና አዜብ መስፍን በኩል የሚገኙት ሰዎችን ለማሳለፍ ከወዲሁ ጥረት እየተደረገ ቢገኝም በስብሀት ነጋና ደብረጽን ገ/ሚካኤል በኩልም ውስጥ ውስጡን ስራ እየተሰራ መሆኑ ተጠቁሞዋል።

በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ አራቱም የወያኔ አባል ድርጅቶች ማለትም ሕወሀት፤ብአዴን፤ኦህዴድ እና ደኢህዴን ለባህርዳሩ ጉባኤ የሚገኙ አባሎቻቸውን መርጠው ማሳወቅ ግዴታ ስለሆነባቸው ከወዲሁ በየቡድኑ ሊወከሉ የሚገባቸውን ለማቅረብ ሽብ ረብ እያሉ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

የህወሀት ስጋት ነው የሚባልለት ኦህዴድ ከሁሉም ቀድሞ በአዳማ በዝግ ስብሰባ ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚሁ ዝግ ስብሰባ ላይ ከጉባኤው በፊት ብዙ ልንነጋገርባቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች ስላሉ አጀንዳ ተቀርፆ ሊቀርብ ይገባል በማለት የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎች እና ከፍተኛ ባለስልጣናት የድርጅቱን ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳን በጥያቄ የስንግ የያዙት ሲሆን ግለሰቡም ጥያቄው ተገቢ ቢሆንም ወቅቱን ያልጠበቀ በመሆኑ ለግዜው እሱን ትተን ለጉባኤ የሚሳተፉትን ብቻ መርጠን እናጠናቅቅ በማለት ሲማጸን መክረሙም ታውቆዋል።

ምንም እንኳዋን አለማየሁ አቶምሳ የካድሬዎቹን ጥያቄ ለግዜው እንተወው የሚል ተማጽኖ እያሰማ ቢሆንም ባለስልጣናቱ ግን አሁን የምናነሳው ጥያቄ በባህር ዳሩ ጉባኤ ላይ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባና መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ እዚሁ ተወያይተን ተማምነን ይዘነው ልንቀርብ የሚገባ ነው በማለት እልህ አስጨራሽ ሙግት ላይ መክረማቸው ታውቆዋል::

በመጨረሻም ጥያቄው ተገቢና ትክክለኛ ቢሆንም ከጉባኤው በፊት ማቅረቡ ለእኛም ሆነ ለድርጅቱ አደጋ ሊያስከትል ስለሚችል ለግዜው ረገብ እንበል በማለት በአለማየሁ አቶምሳ ልመናና ውት ወታ የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቲ አባሎች ጥያቄ የታጠፈ ሲሆን ለባህርዳሩ ጉባኤ የሚሳተፉት ተመርጠው ቀጣዩ ስብሰባ ሚያዝያ ወር መጀመሪያ ላይ ለማድረግ ቀጠሮ ይዘው መበተናቸው ታውቆዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ በወያኔ ሹማምንቶች እና ድርጅቶች መሀከል ሽኩቻው እያየለ በመጣበት በዚህ ግዜ 9ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ለማድረግ በባህር ዳር ከተማ በከፍተኛ ወጪ ልዩ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ታወቀ::

በባህር ዳር ከተማ ለሚደረገው 9ኛ ጉባኤ ከ5 ሺህ በላይ ሰዎች ሊገኙ ይችላል በሚል በከተማዋ ያሉ መለስተኛም ሆነ ትላልቅ ሆቲሎች ሌሎች እንግዶችን እንዳይቀበሉና እንዳያስተናግዱ ከወዲሁ ደብዳቤ የተሰጣቸው ሲሆን ከህዝብ ካዝናም በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ አድርገው እየረጩት መሆኑ ታውቆዋል::

ሕዝቡ በኑሮ ውድነት እግር ከወርች ታስሮና ተጠፍንጎ ባለበት በዚህ ግዜ የወያኔ ቡድን የውስጥ ችግሮቹን ለማርገብና ለማስተንፈስ ብሎም ከአፍሪካ ትልቅና ግዙፍ ፓርቲ እንደሆነ ለማስመሰል የሀገር እና የህዝብ ሀብት ወጪ በማድረግ ድል ያለ ዝግጅት እያደረጉ መሆኑ ታውቆዋል::

የወያኔ 9ኛ ጠቅላላ ጉባኤ በባህር ዳር በሚደረግበት ወቅት በኦህዴድ እና በህወሀት መሀከል ተፈጥሮ የነበረውን የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ውጥረት ለማርገብ ሲባል አንዳንድ ማስተካከያ እንደሚደረግና ወጣት ካድሬዎችም ወደ ማዕከላዊ ምክር ቤት እንዲሸጋገሩ የሚደረግበት ፕሮግራም የተዘጋጀ ሲሆን ከዚህ ሌላ ከውጭ ሀገር የቻይናና መሰል ፓርቲዎች ተወክለው እንዲገኙ እንደሚደረግና ለዚህና ለሌሎች ዝግጅቶች በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ ተደርጎ እየተበተነ እንደሚገኝ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በሕወሀት ክፍፍል ወቅት ከአፈንጋጩ ቡድን ጋር ተመትቶ የነበረውና በሁዋላም ይቅርታ ጠይቆ የመለስን ጉልበት ስሞ የተመለሰው የብአዴኑ ሴኩቱሬ ጌታቸው የቁርጥ ቀን ልጅ ተብሎ ከደኢህዴኑ ባለስልጣን አስተባባሪ ተብሎ በቅርቡ ከተቀመጠው ከሬድዋን ሁሴን ላይ ተቀብሎ ፕሮግራሙን እያንቀሳቀሰ የሚገኝ ሲሆን በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠረው ብር ወጪ የሚደረገውም በዚህ ግለሰብ ስም መሆኑ እያነጋገረ ነው ተብሎዋል::

ብአዴን ከህወሀት...ኦህዴድ ከህወሀት....ጥርስ ተናክሶ አንዴ ሲጠብቅ ሌላ ግዜ ሲላላ የከረመው የእርስ በርስ ችግር በዝግ ስብሰባ ላይ ማዕከላዊ ኮሚቲ ተሰብስቦ በጥልቀት ሳይሆን ላይ ላዩን ሊነጋገርበት እንደሚችልና ለዚህ ጥያቄ ማርገቢያ የሚሆን መጠነኛ ማስተካከያ ሊደረግ እንደሚችል

እየተነገረ ሲሆን ከዋናዎቹ ባለስልጣናት በተጨማሪ ለዚህ ጉባኤ ተመልምለው የመጡ የድርጅቱ አባሎችን አንጀት ለመብላት እና የተባሉትን ሁሉ እንዲቀበሉ ለማድረግ ከፍተኛ ወጪ ተደርጎላቸው በግብዣ እና በአበል ሊንበሻበሹ እንደሆነ የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

በቅርቡ ወደ መድረክ የተመለሰው ሴኩቱሬ ጌታቸው በሚመራው ፕሮግራም መሰረት በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር በስሙ እየተበተነ ከመሆኑም ባሻገር ለሆቲሎች ገና እንግዶቹ ወደ ባህር ዳር ሳይገቡ ቅድመ ክፍያ ተብሎ በመሰጠቱ አልጋዎቻቸው ባዶዋቸውን ለማደር እንደተገደዱና ሌላው ለጉብኝት የሄደው ኢትዮጵያዊም ሆነ የውጭ ሀገር ዜጋ በድንኳዋን ለማደር እንደተገደደ የደረሰን ጥቆማ ገልጾ ጎብኝዎቹ ባጋጠማቸው የአልጋ እጥረት የያዙትን ፕሮግራም እየሰረዙ ወደ መሀል ሀገር እየተመለሱ አንደሆነም ከባህርዳር የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

ትላልቆቹ ባለስልጣናት ለሶስት ቀናት .....መሀከለኞቹ ከአንድ ሳምንት በላይ...... ጭፍሮቻቸው ደግሞ ለ15 ቀናት ተብሎ ከአልጋ እስከ ምግብ ቀድሞ የተከፈለላቸው ሲሆን ትራንስፖርትም ቢሆን ዋናዎቹ አውሮፕላን ትኬት ደርሶ መልስ ሌሎቹም እጅግ ዘመናዊና ምቹ የሆኑ የግለሰብ መኪኖች በኪራይ ተይዘው ሊምነሸነሹበት በዝግጅት ላይ እንደሆኑ የተገኘው ጥቆማ አስረድቶዋል::

ለሀገር እና ለህዝብ ከቶ የማያስበው የወያኔ ቡድን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ የስልጣኑን እድሜ ለማራዘም ሲል ብቻ እጅግ ከሀገሪቱ አቅም በላይ ገንዘብ እየረጨ ህዝቡን ለድህነት ሀገሪቱን ለምድረ በዳነት እየዳረገ መሆኑ የታወቀ ሲሆን አሁንም በተመሳሳይ በሚያሳፍር መልኩ ከባንኮች በግዴታ የወሰደውን ብር ወጪ በማድረግ ካድሬዎቹን ሊያንበሸብሽ መሆኑ አስገራሚ ነው ተብሎዋል::

በሌላ ዜና የተማረ የሰው ኃይል ፍጹም ጠላቱ የሆነው የወያኔ ቡድን በቦንድ ስም የህዝብ ገንዘብ አይዘረፍም ብለው ሲከራከሩ የነበሩትን የአዋሽ ባንክ ፕሬዝዳንት ሰው በመግጨት በሚል የፈጠራ ክስ ወደ ዘብጥያ እንዳወረዳቸው ታወቀ::

የወያኔ ቡድን ከሀገሪቱ ተጨባጭ እና ነባራዊ እውነታ እንዲሁም አቅም ጋር ያልተገናዘበ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ብቻ በጀመረው የተለያዩ ግንባታዎች ምክንያት ለከፍተኛ የገንዘብ እጥረት በመዳረጉ ከሁሉም የግል ባንኮች ውስጥ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር በግዳጅ እንዲያስረክቡ ቢጠየቁም የአዋሽ ባንክ ፕሬዝዳንት አቶ ጸሀዬ ሽፈራው ከፍተኛ ሙግት በመግጠማቸው የተነሳ ጥርስ ተነክሶባቸው የነበረ ሲሆን ባለፈው ሳምንት ውስጥ ሰው በመግጨት ሰበብ ወደ እስር ቤት እንደከተተዋቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

ከ15 ቢሊዮን ብር በላይ ከግል ባንኮች በግዴታ የወሰደው የወያኔ ቡድን አሁንም ገንዘቡ ስላልበቃው በድጋሚ የግል ባንኮች ገንዘብ ወጪ አድርገው እንዲሰጡት ከዓለም አቀፍ ህግ ባፈነገጠ መልኩ አዲስ መመሪያና ደንብ ያወጣ ሲሆን ይህንኑ አሰራር ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበሩት የአዋሽ ባንኩ ፕሬዝዳንት ባለፈው ሳምንት ሰው ገጭተህ አምልጠሀል በሚል ሰበብ ለእስር የተዳረጉ መሆኑ ታውቆዋል::

የወያኔ ኢኮኖሚ ዋነኛ አንቀሳቃሾች ናቸው የሚባሉት የብሔራዊ ባንክ ዋና ኃላፊዎች ያወጡትን ደንብ እና መመሪያ የሚቃወሙትን የአዋሽ እና የሌሎች የግል ባንክ ስራ ኃላፊዎች በደህንነት

ልዩ ክትትል እያደረጉባቸው ሲያስጨንቁዋቸው የነበረ ሲሆን ባለፈው ሳምንት የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም ሰው ገጭተህ ገድለህ አምልጠሀል ተብለው የአዋሽ ባንኩ ፕሬዝዳንት በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሲሆን ሌሎቹ የግል ባንክ ፕሬዝዳንቶችም በጭንቀት ተውጠው እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በቦንድ ስም ከግል ባንኮች 15 ቢሊዮን ብር ከካዝናቸው አውጥተው ሲሰጡ የንግድ ባንክ እና ልማት ባንክ የመንግስት ስለሆኑ አይመለከታቸውም ተብለው ገንዘቡን እንዳይሰጡ የተደረገ ሲሆን በሁለተኛው መንገድ ደግሞ የወጋገን እና አንበሳ ባንኮችም የህወሀት ንብረት ስለሆኑ በተመሳሳይ ገንዘቡን ሳያዋጡ እንደቀሩ ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በአንድ ሀገር የተለያዩ ህጎች የሚተገበሩበት በመሆኑ ሀገርንም ሆነ ህዝብን ይጎዳል እያሉ ሲቃወሙ የነበሩት የግል ባንኮቹ ከዚህ ቀደም 27 በመቶ ቦንድ ግዥ ተብሎ 15 ቢሊዮን ብር የሰጡ ሲሆን አሁን ደግሞ 40 በመቶ በሚል ሌላ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ አድርገው እንዲሰጡዋቸው በደብዳቤ የጠየቁ ቢሆንም ባንኮቹ ከፍተኛ ተቃውሞ እያሰሙ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡